

# የትንቢት ቃል

ወቅታዊ የአድቬንቲስት መጽሔት

ስምንተኛ ዓመት
ቁጥር 2

ሐምሌ 2006

## የሰዎች ነጻ ምርጫ

*በ ዳዊት መሐሪ*

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ ኤፕሪል 2005 «ሳይንቲፊክ አሜሪካን ማይንድ» በተባለው መጽሔት ውስጥ «የአእምሮ ሳይንስ እና ሕግ» በተባለ ርእስ የአእምሮ ጥናት ምርምር ውጤት በዝርዝር ተጽፎ ነበር። ይህንን ምርምር (ሪሰርች) ያደረጉት ሚካኤል ጋዛኒጋ እና ሜጋን ስቲቨን የተባሉት ሊቃውንት ሲሆኑ፤የምርምራቸው ዋና አላማ «በሰው አእምሮ እና አንድ ሰው በማስተዋል በሚያደርገው እንቅስቃሴ (አክሽን) መካከል ያለውን ግንኙነት ለማወቅ ነበር። የእነዚህ ሁለት ሊቃውንቶች ጥናት እ.አ.አ በ1980 ቤንጃሚን ሊቤት በተባለ ፕሮፌሰር ጥናት ላይ የተመሠረተ ነበር። ፕሮፌሰር ሊቤት «አንድ ሰው በማስተዋል እጁን በሚያንቀሳቅስበት ጊዜ በዚያ ሰው አእምሮ ውስጥ የሚካሄዱት ውስጣዊ እንቅስቃሴዎች (አክቲቪቲስ) ምን አይነት ናቸው?» ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት ነበር ምርመራ ያደረጉት። ሊቅ ሊቤት፥ አንድ ሰው ለምሳሌ እጁን ከላይ ወደታች በሚያንቀሳቅስበት ጊዜ በአእምሮው ስለሚከሰቱትን ውስጣዊ እንቅስቃሴዎች ያገኙት ውጤት እንደሚከተለው ነው።

አንድ ሰው እጁን ከማንቀሳቀሱ ከ 500-1000 ሚሊ ሰከንድ በፊት በመጀመሪያ በአእምሮው ውስጥ አንድ እንቅስቃሴ ይካሄዳል። ይህም «እጅህን ለማንቀሳቀስ ተዘጋጅ!» የሚል መልእክት የያዘ እንቅስቃሴ ነው። ፕሮፌሰር ሊቤት በመቀጠል አንድ አእምሮ ይህንን «ተዘጋጅ!» የሚል ውሳኔ ከመቅጽበት ከወሰነ በኋላ ይህንን ከአእምሮ የውስጥ ክፍል የፈለቀውን ውሳኔ (ትእዛዝ/ምክር) ያ ሰው አስተውሎ በተግባር እስኪፈጽመው ድረስ ምን ያህል ሰከንድ እንዳለው በትክክል ለማወቅ ፈለጉ። አንድ ሰው በእነዚህ በሁለቱ እንቅስቃሴዎች መካከል ያለው የጊዜ መጠን 500 ሚሊ ሰከንድ እንደሆነ አገኙ።



ወደ ምርመራው ውጤት መጨረሻ ከመድረሳችን በፊት እዚህ ጋር አንድ ጥያቄ ማንሳት አለብን፥ «እንደዚህ አድርግ! ወይም እንደዚህ አታድርግ!» የሚለው ውሳኔ ከአእምሮአችን የሚመነጭ ከሆነ፤ይህንን ምክር በተግባር ከማዋላችን በፊት (በቃልም ሆነ በተግባር) አእምሮአችን ማድረግ ያለብንን አስቀድሞ ያውቃል ማለት ነው? ይህ እንዲህ ከሆነ ታዲያ የሰዎች ነጻ ምርጫ እድል (ፍሪ ዊል) ምኑ ላይ ነው? ሰዎች በፈቃዳቸው «እሺ» ወይም «እምቢ» ፤ «አዎ» ወይም «አይ» የማለት ምርጫ የላቸውም ፣ እንዲሁ አእምሮአቸው የሚመክራቸውን ምክር ብቻ ተከትለው ነው የሚመሩት ማለት ነው? እስቲ ፕሮፌሰር ሊቤት የደረሱበትን ውጤት እንመልከት።

ምንም እንኳን እጃችንን ለማንቀሳቀስ አእምሮአችን ከወሰነበት ጊዜ ጀምሮ እጃችንን እስክናንቀሳቅስ ድረስ ያለን የጊዜ መጠን 500 ሚሊ ሰከንድ ብቻ ቢሆንም፤እጃችንን እንድናንቀሳቅስ ትእዛዝ ከወጣ በኋላ እስክናንቀሳቅሰው ድረስ ግን 50-100 ሚሊ ሰከንድ ያህል የጊዜ መጠን አለን። ይህም ማለት፥ ከአእምሮአችን የተላከውን ትእዛዝ ለመፈጸም ወይም ላለመፈጸም በግምት 100 ሚሊ ሰከንድ ጊዜ አለን ማለት ነው። እንግዲህ አንድ ሰው በአእምሮው አንድ ሃሳብ ሲመነጭ ይህንን በተግባር ለማዋል ወይም ላለማዋል የነጻ ምርጫ እድል እና ጊዜ አለው ማለት ነው። በመሆኑም እያንዳንዳችን «እሺ» ወይም «እምቢ» ፣ «አደርጋለሁ» ወይም «አላደርግም» ፣ «እናገራለሁ» ወይም «ዝም እላለሁ» የማለት ምርጫ እና ጊዜ አለን።

ለመሆኑ ግን እንዴት ነው አእምሮአችን «ይህንን አድርግ! ወይም አታድርግ!» በማለት ምክርን/ትእዛዝን ሊሰጠን የቻለው? ይህን ሃሳብ ከወዴት አገኘው? ከየትስ አመነጨው?

አንዳንድ ጊዜ ይገርመኛል፥ ሳላስበው በአእምሮዬ የሆነ ሃሳብ ይመጣል። ከዚያ «ይህ ሃሳብ እንዴት ሊመጣ ቻለ?» ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ። መልካም ሃሳብ ከሆነ የመነጨው ደስ ይለኛ፣ ክፉ ሃሳብ ከሆነ ደግሞ በጣም ይጨንቀኝ ነበር። በነገራችን ላይ አንዳንድ ሰዎች (ክርስቲያኖችም እንኳን ሳይቀሩ) ሳያስቡት እንዳጋጣሚ ወደ አእምሮአቸው መጥፎ ሃሳብ ሲመጣ ሰይጣን የሰፈረባቸውና በቁጥጥሩ የያዛቸው ወይም ደግሞ በጣም ኃጥያተኞች ስለሆኑ እንደሆነ ይሰማቸዋል። ይህ የተሳሳተ ሃሳብ ነው! አንድ ሰው ሳይፈልግ ወይም ደግሞ በድንገት ወደ አእምሮው ክፉ ሃሳብ መጣ ማለት ያ ክርስትያን በዚያች ሰዓት ሰይጣን ሰፍሮበታል ወይም እሱ ችግር ስላለበት ነው ማለት አይደለም። ያ ሰው ችግር የሚኖርበት የመነጨውን ይህንን ክፉ ሃሳብ በማስተናገድ ቀጥሎም በተግባር በማዋል እርምጃ ከወሰደ ነው። ይህንን ሀቅ ለመረዳት የሰው አእምሮ

*(በገጽ 4 ይቀጥላል)*

**በዚህ እትም ውስጥ**


| | |
|---|---|
| *የሰዎች ነጻ ምርጫ* | 1 |
| *ከአዘጋጆች* | 2 |
| *ራእይህን አስፋ!* | 2 |
| *የአድቬንቲስት እምነት ወደ መቀሌ (ትግራይ) እንዴት ገባ?* | 3 |
| *ምን መብላት እንደሚሻል* | 4 |
| *ሰባቱ መለከቶች (ክፍል 2)* | 5 |
| *የመከራ ዘመን (ክፍል3)* | 6 |
| *ቃለ መጠይቅ ከወንጌላዊ ባህሩ ወ/ገብርኤል ጋር* | 7 |
| *ከአንባቢዎች* | 8 |



## ከአዘጋጆች

***የተወደዱ አንባቢ ሆይ!***

በቅርቡ እድሜው ስምንት ዓመት ከሆነው ወንድ ልጄ ጋር በመኪና እየሄድን ሳለን በአድናቆት ስለአንድ ነገር ያጫውተኝ ጀመር። የአነጋገሩ ሁኔታ እና ከፊቱ የሚታየው ደስታ በጣም አስገረመኝ። ያጫውተኝ የነበረው በወቅቱ በመላው ጀርመን ዋና የመነጋገሪያ ርዕስ ስለነበረው ስለ ዓለም አቀፍ የእግር ኳስ ጨዋታ ውድድር ነበር። የዘንድሮውን ውድድር ያስተናገደችው አገር ጀርመን ስለነበረች ከተሞችዋ ሁሉ በተለያዩ ባንዲራዎች አሸብርቀዋል፤ከመላው ዓለም የመጡት እንግዶችም የየቡድናቸውን ማሊያ ለብሰው አካባቢውን ሲያደምቁት ነው የሚታየው። እለት በእለት ይህንን የሚመለከተው ልጄ በዚያ ቀን ከትምህርት ቤት ሲመለስ በአድናቆት የትኛው ቡድን የትኛውን እንዳሸነፈ፣ነብይ ይመስል ደግሞ በመጨረሻ የትኛው ቡድን ዋንጫውን እንደሚወስድ እየነገረኝ ወደ አሰብንበት ስፍራ ደረስን።

ይህ ከሆነ ከጥቂት ቀናት በኋላ ለብቻዬ በጸሞና ጊዜ ላይ ሆኜ ስለ ንግግራችን ሳስብ ሳለሁ አንድ ነገር አስተዋልኩ፥ ለካስ አንድ ሰው የሚያየው እና ሁልጊዜ የሚሰማው ነው በእለት ሕይወቱ ሲንጸባረቅ የሚታየው! ከአፍ የሚወጣውም ሆነ በተግባር የሚታየው አንዴ ወደ ልብ የገባው ነገር ነው። አእምሮአችንን (ልባችንን) የመገብነውን ያንን ነው በሕይወታችን የምናንጸባርቀው።

እንግዲህ የሐዋሪያው ጳውሎስ ምክር ከመቼውም የበለጠ እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ እንመልከታለን፥ «እኛም ሁላችን በተገለጠ ፊት የጌታችንን ክብር እያየን፤እንደመስታወት እያንጸባረቅን የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን» (2 ቆሮ 3፥18)።

ውድ አንባቢ ሆይ፥ በአድቬንቲስት የውዳሴ መጽሐፍ ውስጥ «ወደ የሱስ ተመልከት ግሩም አስደናቂ ፊቱን የዚህ ዓለም ሃብት ሁሉ ጠፊ ነው ሁሉም ያልፋል ግርማውን ስናይ» የሚል መዝሙር አለ። ለልጄም ሆነ ለእኔ እንዲሁም ለእርስዎ የምመኘው የእምነታችንን ጀማሪና ፈጻሚ የሆነውን ጌታ የሱስን ሁልጊዜ እየተመለከትን በዚህ ምድር ላይ እርሱን እንድናንጸባርቅ ነው።

የእናንተው

***ዳዊት መሐሪ***

ወንጌል

## ራዕይህን አስፉ!

እግዚአብሔር በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ታላቅ ነገርን ሊያደርግ ተዘጋጅቶአል፣ ያንንም እንድናውቅ፣ እንድንጠባበቅ፣ እንድናምን ይፈልጋል፤ እምነት እግዚአብሔር ለሰው ያለው በጎ ሃሳብ ሥር እንዲሰድና እንዲያድግ ያደርገዋል:: በትንቢተ ኤርምያስ 29:11 «ለእናንተ የማስባትን እኔ አውቃለሁ ይላል እግዚአብሔር የሠራዊት አምላክ....» ካለ በኋላ ሃሣቡ የክንውን የበጎ ነገር፣ የተስፋ ሃሳብ እንደሆነ ይናገራል:: ይህንን ቃልኪዳኑን ካልረሳን ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር በጎ ነገርን የምንጠባበቅ፣ በቀላሉ ተስፋ የማንቆርጥ፣ ራሳችንን ምስኪኖች ከሰው በታች የሆንን አድርገን የማንመለከት ነገር ግን እግዚአብሔር በጎ ነገርን የሚያደርግልን፣ በችግርና በፈተና ሁሉ ድል ነሺዎች የሚያደርገን እንደሆንን አድርገን እናያለን፣

ለዚህ ነው በኢሳይያስ... ኢሳ. 43:19 «እነሆ አዲስ ነገርን አደርጋለሁ እርሱም አሁን ይበቅላል እናንተም አታውቁትምን? ካለ በኋላ «በምድረበዳ መንገድን በበረሃም ወንዞችን አደርጋለሁ»:: ያለው በዚህ አነጋገሩ እግዚአብሔር በተስፋው ሊሞላን ይፈልጋል፣ በማንኛውም ዓይነት ችግር ውስጥ ሆነን ራሳችንን ብናይ ይህ ቃል የተስፋንና የድል አድራጊነትን ብርሃን በህይወታችን እንዲበራ ያደርጋል:: በሕመም የምንማቅቅ ብንሆን በዚህ ተስፋ የፈውስ አምላክን እንመለከታለን፤ በተለያዩ አጉል ልምዶች የተያዝን ብንሆን አዲስ ነገርን በሚያደርግ አምላክ ነፃ የመውጣት ብሩህ ተስፋን የተሞላን እንሆናለን:: በበረሃ ወንዝ ወይም በምድረበዳ መንገድ በሰው አመለካከት የሚታሰብ ነገር አይደለም፣ እግዚአብሔር ግን በሰው ሊታሰብ የማይችለውን ሊያደርግ የሚችል አምላክ ነው፣ ብዙ ጊዜ የምንቸገረው ከእግዚአብሔር ጋር አለስማማ እያልን ነው፣ ከእርሱ ጋር ብንስማማ እርሱ ያለውን እናምናለን፣ እርሱ ያለውን ካመንንና ከተቀበልን ደግሞ በችግር ውስጥ ሁነን ከችግር መውጣትን እንመለከታለን፣ ሁልጊዜ በእግዚአብሔር በጎነት ሥር እንዳለን ስለምናውቅ ምንም ዓይን ችግር አያሸንፈንም::

ስለዚህ ይህን ለምናነበው ሁሉ እግዚአብሔር እንዲህ እያለን ነው እነሆ እኔ አዲስ ነገርን (አንተ ወይም አንቺ ሊሆን ይችላል ብለህ/ሽ ያልጠበቅከውን) አደርግልሃለሁ፣ አታስተውሉምን? ይላል፤ እግዚአብሔር ሁልጊዜ አዲስ ነገርን ታላቅ ነገርን በህይወትህ ሊያደርግ ተዘጋጅቶአል፣ ሊያሳድግህ ሊያበዛህ ድል አድራጊ ሊያደርግህ ወዘተ.. ግን ይህንን እናውቅ እንደሆነ፣ እናምንና እንስማማ እንደሆነም ይጠይቀናል::

በእግዚአብሔር በማመንና ከርሱም ጋር በመስማማት ራዕያችንን እናሰፋ◆

***አገኙሁ ወንድም (ፓስተር)***
***ከአዲስ አበባ ኢትዮጵያ***

ድህረ ገፃችንን ይጎብኙ!
www.yetnbitkal.org





# የአድቬንቲስት እምነት ወደ መቀሌ /ትግራይ/ እንዴት ገባ?

በ1948 ዓ.ም አካባቢ አንድ የሆነ ሰው ከአዲስ አበባ እየመጣ መኪና ውስጥ ላገኛቸው የመቀሌ ነዋሪ ለሆኑ አለቃ ጴጥሮስ ለተባሉ ግለሰብ አንዲት የትንቢት ድምፅ ይሰጣቸውና አንብበው ለባሻይ ስቋር ለተባሉ ሰው ይሰጧቸዋል፡፡ ባሻይ ሰቋርም ካነበብዋት በኋላ ለአለቃ ኃይሉ ተሰማ ይሰጥዋቸዋል፡፡

አለቃ ኃይሉ ተሰማ የ4ኛ ዮሃንስ ትምህርት ቤት (በአሁኑ አጼ ዮሐንስ የሚባለው) የአማርኛ መምህር ሲሆኑ በ1948 ዓ.ም. በየአመቱ መጨረሻ በክረምት ወራት የአማርኛ ኮርስ ለማድረግ ወደሚሄዱበት ወደ አዲስ አበባ ይሄዳሉ ሲሄዱም ያችን ያገኟትን የትንቢት ድምፅ ይዘዋት ይሄዱና ኮርሳቸውን እንደጨረሱ ወደ ፍልውሃ አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ሄደው ተከታታይ የትንቢት ድምፅ በመያዝ ወደ መቀሌ ተመልሰው መፅሐፍ ቅዱስን እያነበቡና እያጠኑ የተሰጡትን ጥያቄዎች ከመለሱ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በመላክ አሳርመውት በሰጡት አጥጋቢ መልስ ሽልማት አግኝተውበታል፡፡ በቀጣዩ አመት አሁንም ለአማርኛ ኮርስ ወደ አዲስ አበባ እንደሄዱ ጌታ የሱስን የግል አዳኛቸው አድርገው በመቀበል ተጠምቀው ተመለሱ፡፡ ወዲያውም በዚሁ ዓ.ም. የአማርኛ መምህርነታቸውን ለቀው የወንጌል መምህር ሆነው እንዲሰሩ ተቀጠሩ፡፡ ለተወሰኑ አመታት በወንጌላዊነት በመቀሌ ከተማ ከሰሩ በኋላ ያላቸው ችሎታ ተገምግሞ የፓስተርነት ቅባት ተቀቡ፡፡ የመቀሌ አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ሃላፊ ሆነውም ማገልገል ጀመሩ፡፡ በመቀሌ ከተማ ካሉ ጥንታዊ አድቬንቲስታዊ ፈር ቀዳጆች (pioneers) መካከል የመጀመሪያው ሰው ፓስተር ኃይሉ ሲሆኑ እሳቸውም ባደረባቸው ህመም ምክንያት ሊሰሩ የተገባቸውን አምላካዊ ሥራ በመሥራት በ1972 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡ ከሳቸውም በኋላ ፓስተር ሃይሉ ካተረፏቸው በህይወት ካሉት ጥንታዊያን አድቬንቲስት ፈር ቀዳጆች (pioneers) መካከል መምህር ገብሩ ተገኝና መምህር ቀለም ለገሰ ዛሬም የቤተክርስቲያናችን ጌጥ ሆነው በሕይወት የሚገኙ ሲሆን መምህር ቀለም ለገሰ ዛሬም በትግራይ ሚሽን ውስጥ ያገለግላሉ፡፡



Yohaness Palace

ይህ በእንዲህ እንዳለ የምናደርገው የመፅሃፍ ቅዱስ ጥናትና የፀሎት ፕሮግራሞች እንዲሁም ሰንበት ሰንበት የምናደርገው የአምልኮ ፕሮግራም የሚካሄደው በፓስተር ኃይሉ ተሰማ መኖሪያ ቤት ውስጥ ነበር፡፡ በዚያው ዓመት የምእመናን ቁጥር አስር ያህል ደረሰ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአዲስ አበባ ሊጎበኙን የመጡ ወንጌላዊ አቶ አሉላ ዋሴ የሚባሉ ነበሩ፡፡ ጥሩ የማፅናኛ ቃል ያለበትን የእግዚአብሄር ቃል በማስተማር አነቃቅተውንና አደፋፍረውን ተመለሱ፡፡ በመቀሌ ከተማ የአድቬንቲስት እምነት በጥሩ ሁኔታ እየተስፋፋ መሆኑን የሰሙ የኢትዮጵያ አድቬንቲስት ዩንየን መሪዎችም በኤርትራ ካለው ሥራ ጋር የነሱ ቅርንጫፍ ሆነን እንድንሰራና የኢትዮጵያ አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን የሰሜን ኢትዮጵያ ሰበካ እኛን ተቀብሎ አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያደርግ፣ በየጊዜውም ወደኛ እየመጡ እንዲያስተምሩን፣ እንዲያበረታቱንና እንዲከታተሉን ትእዛዝ አስተላለፈላቸው፡፡ በዚህም መሰረት የሰሜን ኢትዮጵያ ሰበካ ፕሬዚደንት የነበሩት ፓስተር ተበጀ ጉዳዬ በዚያን ጊዜ ወንጌላዊ ከነበሩት ፓስተር አምደብርሃን ማና ጋር ሊጎበኙን መጡ፡፡ ያገኙንም በፓስተር ኃይሉ ተሰማ ቤት ነበር፡፡ የእግዚአብሄርን ቃል ካሰሙን በኋላ ፓስተር ተበጀ እንዲህ አሉ፡ "ለምን እዚህ ታምቃችሁ ታመልካላችሁ? እውነቱ ለመቀሌ ከተማ ህዝብ ይውጣ በሉ አሁን ውጡና ሰፋ ያለ የሚከራይ ቤት ፈልጉና እዛ ሆነን ወንጌልን እንግራለን ህዝቡም ይወቅ የፈለገ መጥቶ ይስማ ይማር እናንተም ውጡና አድሙት (ጥሩት) ና እና እይ በሉት" አሉ፡፡ እኛም እንዳሉት ቤት ለመፈለግ ባደረግነው ጥረት በመሃል ከተማ ፒያሳ አጠገብ ጥሩና ሰፊ ቤት ሁለት ክፍል ያለው አገኘን፡፡ ፓስተር ተበጀም አዩትና ደስ አላቸው ሰፊው ክፍል መሰበኪያ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የነሱ ጊዜያዊ መኖሪያ አደረጉት፡፡ ከገበያ ሰሌን ገዝተን ወለሉ ላይ አንጥፈን እኛና የሚመጡት የታደሙ እንግዶች በሰሌኑ ላይ በመቀመጥ ስብከቱ ቀጠለ፡፡ እረዳታቸው ፓስተር አምደብርሃንና ፓስተር ተበጀ ጉዳዬ በመተጋገዝ ለአሥር ቀናት የሚሆን ትምህርት ሰጡን፡፡ ትምህርቱ በሚካሄድበት ጊዜም የድንጋይ ውርወራ አላቋረጠም፡፡ ድንጋዩ ይወረወራል፣ ይሰድቡናል ቢሆንም የወንጌሉ ትምህርት የሚያግደው ነገር አልነበረም፡፡ ነቀፌታ፣ ስድብ፣ ጥላቻ ከዚህም የተነሣ በቤቱ ጣራ ላይ የድንጋይ ናዳ ይወርድብን ነበር፡፡ ጻሩ ግን ምንም ቢሆን ምንም ሊያስበረግገን አልቻለም፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሄር በህይወታችን ላይ አደጋ እንዳይደርስብን ይከላከልልን ስለነበር ነው፡፡ የኋላ ኋላ እነ ፓስተር ተበጀ ወደ ምድብ ስራቸው ወደአስመራ ሲመለሱ እኛም ወደነበርንበት ወደ ፓስተር ሃይሉ ቤት በመመለስ የተለመደውን አምልኮአችንን ቀጠልን፡፡ ጥቂት ዓመታት በእንደዚህ አኳኋን እንደተጓዝን በሰሜን ኢትዮጵያ ሰበካ የነበሩ ሃላፊዎች ችግራችንን ስለተገነዘቡ የምናመልክበት ቦታና ቤት በቀበሌ 16 ተገዛልን፡፡ እፎይ በማለት አምላካችንን እያመሰገንን በጣምም ደስ እያለን ረቡዕ፣ ዓርብና ሰንበት ዕለት በአዲሱ ቤት ፀሎታችን እየተገናኘን ምንም እንኳን ያ የድንጋይ ውርወራ የቀጠለ ቢሆንም አምልኳችንን ቀጠልን፡፡ የኋላ ኋላ ግን እየለመድነው መጣን ጌታም ፅናቱን ሰጠን፡፡ ምንም አይነት ድንጋጤ ወይም ሽብር አይሰማንም ነበር፡፡



Mekele Institute of Tech-

አሁን ያለንበትን የማምለኪያ ቤት (ቤተ ክርስቲያናም) ያገኘንበት ምክንያት ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ የሰሜን ኢትዮጵያ ሰበካ ፕሬዚደንት ሆነው የተመረጡት ፓስተር ብርሃነ ወልደ ማርያም መቀመጫቸውን በመቀሌ ከተማ በማድረግ ሥራቸውን ሲሰሩ ስለነበረ ሲሆን በብዙ ትግልና ጥረት በምሪት ስም ከመንግስት ቦታ ካገኘን በኋላ ፓስተር ብርሃነ ወዲያው በውጪ አገር ከሚገኙ በጎ አድራጊዎች (ለጋሽ አገሮች) በመፃፍ ቤተክርስቲያን የሚሰራበት የገንዘብ እርዳታ በመጠየቅ በተገኘው ገንዘብ ስራው ተጀመረ፡፡ ቢሆንም በእርዳታ የተገኘው ገንዘብ ቤተክርስቲያኑን ለማሰራት ስላልበቃ የሰሜን ኢትዮጵያ ሰበካ በቀበሌ 16 ገዝቶልን ስናመልክበት የነበረው ቦታና ቤት ተሸጦ ይህ አሁን የምናመልክበት ቤተክርስቲያን እንዲጠናቀቅ ሆነ፡፡ የቤተክርስቲያኑም ሥራ በ1970 ዓ.ም. የተጠናቀቀ ሲሆን እስካሁንም ያለነው በዚያው ቤት ነው፡፡ የጌታ ስም የተባረከ ይሁን፡፡◆

**ፓስተር አብርሃም ተካ**

**የትግራይ ሚሽን ፕሬዚደንት**

**ምንጭ፡ መምህር ቀለም ለገሰ**

(25/05/1998 ዓ.ም.)



# ምን መብላት እንደሚሻል

በጥሩ አመጋገብ አካሉ የተገነባ ሰው ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የሚያዘወትርና ሳያለሰልስ የጤናማ አኗኗር ፕሮግራም የሚከተል ከሆነ 1) ጠንካራ ይሆናል፣ 2) አጥንቶቹ ጠንካራና ትክክለኛ ቅርጽ ይኖራቸዋል፣ 3) ጡንቻዎቹ የዳበሩና ጠንካራ ይሆናሉ፣ 4) የአካል ቅልጥፍና ይኖረዋል፣ 5) የአካሉ አጠቃላይ ቅርጽ አስደሳች ይሆናል።

ኅብረሕዋሳትን ለመገንባትና ለመጠገን አስፈላጊ የሆነው ፕሮቲን በምግብ ውስጥ በበቂ መጠን መገኘት የተሟላ ጤንነት ለማግኘት በከፊል አስተዋጽኦ ያደርጋል። የአካል ኅብረሕዋሳትን ለማጠንከር በቂ ማእድን በምግብ ውስጥ መኖር አለበት፣ማእድን ጥርስንና አጥንትን ለመገንባትና ለመጠገን ይረዳል። ጉልበት ወይም ኃይል ለማግኘት በቂ ካርቦሃይድሬትና መጠነኛ ቅባት በምግብ ውስጥ መኖር አለባቸው። ኅብረሕዋሳትን በጥሩ ሁናቴ ለመጠበቅና አንጎል፣ነርቮችና ሌሎችም ዋና የአካል ብልቶች በትክክል ሥራቸውን ለማካሄድ እንዲችሉ ቫይታሚኖች አስፈላጊ ናቸው።

በጥሩ ሁኔታ መመገብ ማለት ለአካል የሚያስፈልጉ የምግብ አይነቶችን በተመጠነ ብዛትና አይነት መመገብ ማለት ነው።

## የተለመዱ የአመጋገብ ስህተቶች

እጅግ በጣም ተስፋፍቶ ለሚገኘው የአመጋገብ ጉድለት ዋና ምክንያት የሆኑ ቢያንስ አምስት የአመጋገብ ልምዶች አሉ። እነዚህ ልምዶች የአመጋገብ ስህተት የሚሠሩ ሰዎች ጥንካሬና የተሟላ ጤና እንዳያገኙ የሚያደርጉ የቅጣት መሳሪያዎች ናቸው። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፤ 1) ያለመጠን መብላት 2) ከመመገቢያ ሰዓት ውጪ መብላት 3) ብዙ ስኳር እና ስኳር ያለባቸውን ምግቦች መብላት 4) በፋብሪካ የሚዘጋጁ ምግቦችን ከመጠን በላይ መመገብ 5) ቁርስን ችላ ማለት።

## ጉልበት ሰጪ ምግቦች

ጉልበት ሰጪ ከተባሉት የምግብ አይነቶች መካከል አብዛኛው ፕሮቲን፣ ካርቦሃይድሬትና ቅባት ናቸው። የጉልበት ሰጪ ምግቦች መጠን ከግለሰቦች የእንቅስቃሴ ብዛትና ማነስ አንጻር እየታየ መጨመርና መቀነስ አለበት። እንዲሁም ጉልበት ሰጪ ምግቦች ከሰውነት ግዙፍነትና አነስተኛነት አኳያ መስተካከል አለባቸው። የጉልበት ሰጪ ምግቦች መጠን እንደተመጋቢው የእድሜ ደረጃ ይለያያል። የተመጋቢው ግለሰብ ክብደት የመጨመር አዝማሚያ ከታየበት የጉልበት ሰጪ ምግቦችን መጠን መቀነስ ያስፈልጋል።

በየቀኑ የሚያስፈልጉ የምግብ አይነቶች በአራት ይመደባሉ። ይህ አመዳደብ አንድ ሰው የተመጣጠነ ምግብ ለማግኘት እንዲችል የሚረዳ ቀላል ዘዴ ነው። በየቀኑ መበላት ወይም መጠጣት ያለበት የምግብ ዝርዝር

1) ወተት ወይም የወተት ምርቶች
2) ፕሮቲን (ለውዝ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ምስር፣ እንቁላል፣ አሳ፣ የአእዋፍ ሥጋ፣ የከብት ሥጋ ወይም የሥጋ ምትኮች)
3ኛ) አትክልትና ፍራፍሬ
4ኛ) የዳቦ እና የጥራጥሬ እህል።

ታዋቂነት ባለው ስለ ምግብ በተማረ ሰው የተዘጋጀ የምግብ ዝርዝር (ሜኑ) መሰረት መመገብ ወይም ደግሞ ብዙ የምግብ ዝርዝሮች ከመጻሕፍትና ከመጽሔቶች ማግኘት፣ከሃኪሞችና ከትምህርት ቤት መጋቢዎች አስተያየት መሰብሰብና በዚያ መመራት ይቻላል። ◆

*ምንጭ፥ ሆሀተ ጤና፤ገጽ 76–83*

---

*(የሰው ነጻ ምርጫ ከገጽ1 የዞረ)*

እንዴት እንደሚሠራ ማወቅ ይጠቅማል። አእምሮ በስሜት ሕዋሳቶቻችን የምናደርጋቸውን (የምንለማመዳቸውን) ነገሮች ሁሉ የመቅረጽ ወይም ሰብስቦ የማስቀመጥ (ሜሞራይዝ የማድረግ) ችሎታ አለው። ከሕጻንነታችን ጀምሮ የምናያቸው፣የምንሰማቸው፣የምንዳስሳቸው እና የምናሸታቸው የእለት ከእለት ልምምዶች በአእምሮአችን ይቀረጻሉ። በተለይ የቀድሞ ልምምዳችን እጅግ በጣም ስሜትን የሚነካ ልምምድ ከነበረ ትዝታው በአእምሮአችን ለረጅም ጊዜ እንደተቀረጸ ይቆያል። ከረጅም ጊዜ በኋላ ተመሳሳይ ሁኔታ ሲያጋጥመን ያ የቀድሞው ልምዳችን ትዝ ይለንና በዚያ ወቅት የምንወስደው እርምጃ አእምሮአችን ያኔ እንድናደርግ የመከረንን አይነት ምክር ይሆናል። ስለዚህ በእያንዳንዱ ገጠመኞቻችን አእምሮአችን ከዚህ ቀደም ከቀረጸው ሁኔታ ጋር ያነጻጽርና «ይህንን አድርግ» ወይም «አታድርገ» የሚል ምክር ይሰጠናል። እንግዲህ ይህ ማለት ከአእምሮአችን የሚመነጩት ምክሮች ከዚህ በፊት በተቀረጹት (ሜሞሪስ) ይወሰናሉ ማለት ነው። አእምሮአችን የሚሰጠንን ምክር በተከተልን መጠን ደግሞ ይህ ምክር ትክክል እንደሆነ ለአእምሮአችን የበለጠ እያረጋገጥንለት፣ወደፊትም በተመሳሳይ ሁኔታ ተመሳሳይ ምክር እንዲሰጠን እያጠናከርንለት እንሄዳለን ማለት ነው። የሚሰጠንን ምክር ግን የምንቃወምና በዚያ ፈንታ ሌላ እርምጃ የምንወስድ ከሆነ ደግሞ አእምሮአችን ወደፊት የቀድሞውን ምክር እንዳይሰጠን እያዳከምነው በዚያ ፈንታ የተሻለ ምክርን እንዲሰጠን እያሰለጠንነው ነው ማለት ነው።

እንግዲህ ውድ አንባቢ፥ ሊቃውንቶቹ በምርምራቸው ያገኙት ውጤት ይህንን ይመስላል። ታዲያ ይህ ለእኛ ለክርስቲያኖች ምን ትምህርት ይሰጠናል?

በእርግጥ ከአምሮአችን በሚፈልቁት ምክሮች ላይ በቀጥታ ተጽእኖ ማድረግ አንችልም፣ቢሆንም ወደ አእምሮአችን ምን መከማቸት (መቀረጽ) እንዳለበት ተጽእኖ ማድረግ እንችላለን። የምናየውንና የምንሰማውን በመምረጥ አእምሮአችንን ጠቃሚ ምግቦች መመገብ እንችላለን። በምንኖርበት በአሁኑ ዘመን ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ፣ ኢንተርኔት እንዲሁም ሌሎች የጎልማሶችና እና የህጻናት መጫወቻዎች (ጌይምስ) በመላው ዓለም እየተስፋፋ ባለበት ወቅት በማስተዋልና በጥንቃቄ የምናየውንና የምንሰማውን በመምረጥ እራሳችንን እየገዛን ካልኖርን በእለት ሕይወታችን ክፉ ገጠመኞች ቢያጋጥሙን ወይም ደግሞ የተመሰቃቀለ ሕይወት ቢኖረን ሊያስገርመን አይገባም። ምክንያቱም አእምሮአችንን በመገብነው በዚያ መጠን ነው ምክርን የሚያመነጨው። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሊረዱን ይችላሉ፤

«በጽድቅ የሚሄድ፣ ቅን ነገርንም የሚናገር በሸንገላ የሚገኝ ትርፍን የሚንቅ፣መማለጃን ከመጨበጥ እጁን ከሚያራግፍ፣ደም ማፍሰስን ከመስማት ጆሮቹን የሚያደናቁር፣ ክፋትንም ከማየት ዓይኖቹን የሚጨፍን ነው። እርሱ ከፍ ባለ ስፍራ ይቀመጣል ጠንካራ አምባ መጠጊያው ይሆናል እንጀራም ይሰጠዋል ውኃውም የታመነች ትሆናለች።» (ኢሳያስ 33፥15-16)

**እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።** (ሮሜ 12፥1-2)

ምንም እንኳን አእምሮአችን ክፉ ምክር ቢሰጠንም ይህንን ምክር ለመቀበል «እምቢ» የማለት ምርጫ ተሰጥቶናል። አለበለዚያ ያእቆብ በመልእክቱ የጻፈውን በሕይወታችን ስንፈጽም እንገኛለን፤

*(በገጽ 6 ይቀጥላል)*



# ሰባቱ መለከቶች (ክፍል 2)

ይህ ትምህርት በራእይ ምእራፍ 9 ላይ የተመሠረተ ነው

ባለፈው እትማችን በራእይ ምእራፍ 8 ላይ የተዘረዘሩትን የመጀመሪያ አራት መለከቶች ተመልክተናል። በዚህ እትም ደግሞ ባለ ራእዩ ዮሐንስ «በምድር ለሚኖሩት ወዮላቸው፣ወዮላቸው፣ወዮላቸው» ተብሎ በታላቅ ድምጽ ስለሰማቸው ስለ ሶስቱ ወዮዎች እንማራለን። ራእይ 9፥1-21 በቅድሚያ ያንብቡ እና ጥያቄዎቹን ይመልሱ።

1. በትንቢት «ከዋክብት» ሲል ማንን ለመግለጽ ነው? (ራእይ 1፥20)

2. ከሰማይ ወደምድር ለወደቀው ኮከብ ምን ተሰጠው? (ራእይ 9፥1)

ይህ የወደቀው መልአክ ወደ ምድር እንደ መጣና የጥልቁ ጉድጓድ መክፈቻ እንደተሰጠው እናያለን። ጉድጓዱ እንግዲህ ያለው በዚህች ምድር ላይ ነው ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ዘወትር የጨለማ ኃይሎች በዚህች ምድር እና አካባቢዋ ላይ ብቻ መወሰናቸውንና ከጥልቁ ጉድጓድ ሲወጡ እንደሚገልጽ እናያለን። ስለዚህ ጉድጓዱ ይህ ክፉ ዓለም እንደሆነ ግልጽ ነው።

3. ይህ የወደቀው መልአክ ማነው? (ራእይ 12፥9 ሉቃስ 10፥18)

4. የጥልቁንም ጉድጓድ ሰይጣን እንዲከፍት በተፈቀደለት ጊዜ ምን ሆነ? (ራእይ 9፥2)

5. ከጪሱ የተነሳ የጨለመውስ ምንድን ነበር? (ራእይ 9፥2)

6. በዚህ ትንቢት ውስጥ በዋናነት የሚጠቀስ ተባይ ምንድን ነው? (ራእይ 9፥3)

እነዚህ ተባዮች የተለመዱ አንበጣዎች አይደሉም። ምክንያቱም ተራ አንበጣዎች አይናደፉም። እነዚህ ከአንበጣ የበለጠ እንደጊንጥ ያሉ ተባዮች ናቸው። እነርሱም የሴት ጠጉር በሚመስል ጠጉራቸው ላይ የወርቅ ዘውድ ጭነው ነበር። ቅርጻቸውም ለጦርነት እንደ ተዘጋጁ ፈረሶች ነበር (ራእይ 9፥7-8)። እነዚህ በትንቢታዊ አነጋገር የተጠቀሱት የበረሃ አንበጣዎች የእስላምና ሃይማኖት በምድር ላይ ከመስፋፋት ጋር እንደሚገናኝ የስነ መለኮት ሰዎች ይናገራሉ። እስልምና በሰሜን አፍሪካ፣በስተምእራብ እስከ እስፔይን ድረስ በስተሰሜን ደግሞ እስከ ኤሽያ ማይነር (ቱርክ) ድረስ፣በምስራቅ አቅጣጫ ደግሞ ከኢራን እስከ ፓኪስታንና ህንድ ድረስ ከ60 የተለያዩ ሃገሮች በላይ ተስፋፍቶአል። (ዋቢ፥ ጎድ ኬርስ ገጽ 246)።

7. እነዚህ አንበጣ መሳይ ጊንጦች እንዲጎዱ የተነገራቸው ማንን ነበር? (ራእይ 9፥4)

8. ይህ ስቃይ ምን ያህል ጊዜ ቆየ? (ራእይ 9፥5)

በትንቢት ቋንቋ አንድ ቀን እንደ አንድ ዓመት ስንጠቀም በወር ሰላሳ ቀናት ያሉት አምስት ወራት በትክክል 150 ዓመታት ናቸው። «ኤድዋርድስ ጊቦንስ» የተባሉ አንድ የታሪክ ሰው እንዳሉት ከሆነ የኦቶማን ቱርኮች መጀመሪያ የግሪክን መንግሥት ወይንም ሊቶዲሚያን የወረሩት እ.አ.አ. ሐምሌ 2/1299 ዓ.ም. ነበር። ከዚያ ወረራ ጀምሮ ለ150 ዓመታት የማያቋርጥ ጦርነት አካሄዱ። ንጉሣቸውም አባዶን ወይም አፖሊዮን (አጥፊ) ይባል ነበር።



9. እነዚህ ጊንጦች ከአካላቸው በየትኛው ክፍል ነበር የሚናደፉት? (ራእይ 9፥10)።

የእስላም ተዋጊዎች የታወቁ ፈረሰኞች ነበሩ። ረዥም ጸጉራቸውን ከቆባቸው በታች አንዠርግገው ወደ ጠላቶቻቸው በፈረስ ቀጥ ብለው ይሮጡና ወደ ኋላቸው በመመለስ የሚሸሹ ያስመስላሉ። ይህን ያየው የጠላት ኃይል ሲዘናጋ በፈረሶቻቸው ጭራ ላይ ያደረጉትን ጨርሶ አጥፊ የሆኑ ቀስቶቻቸውን ያፋፍሙባቸዋል።

10. ለሚቀጥለው ወዮ እንደ መነሻ ሆኖ የተጠቀሰው ወንዝ የትኛው ነበር? (ራእይ 9፥13-14)።

11. ሁለተኛው ወዮ ምን ያህል ጊዜ ነበር የቆየው? (ራእይ 9፥15)

በረዶና እሳት እንደ ነጎድጓድ ያሉትን ጦርነቶች የሚያሳይ ቅኔአዊ መግለጫ ነው። በረዶ እሳትና ደም በአንድነት ሲወሰዱ ጦርነትን ያንጸባርቃሉ። ከተገኘው ለምለም ነገር ሲሰው የሚያሳየን፤ ዓለም አቀፍ ጥፋት ያስከተለን ጦርነት ባይሆንም ታዋቂ የጦርነት ድርጊትን ነው። (ዋቢ፥ ጎድ ኬርስ ገጽ 236)። የጊዜው ስሌት እንደሚከተለው ነው፥ አንድ ሰዓት=15 ቀናት፣አንድ ቀን=አንድ ዓመት፣አንድ ወር=30 ዓመታት፣አንድ ዓመት=360 ዓመታት። አጠቃላይ ድምር 391 ዓመታት ከ15 ቀናት ናቸው። እ.አ.አ. ከሐምሌ 27/1299 እስከ 1449 ድረስ 150 ዓመታት (5ወራት)፤ከ1449 እስከ ነሀሴ 11/1840 ድረስ 391 ዓመታትና 15 ቀናት ናቸው። ጆሴፍ ሊች የተባለ የፕሬስቢቴሪያን ቤ/ክ አገልጋይ ከ1840 ሁለት ዓመት ቀደም ብሎ ከዚህ ትንቢት በመነሳት የኦቶማን ግዛት በ1840 ይወድቃል በማለት አንድ ጽሑፍ አሳተመ። በተጨማሪ ድርጊቱ ከመፈጸሙ ጥቂት ቀደም ብሎ ጊዜው ነሐሴ 11 እንደሚሆን አወጀ። እንደዚህ አይነቱን ድፍረት ሰዎች አጣጣሉት። ነገር ግን ሱልጣኑ (ንጉሡ) በዚህ በተተነበየው ቀን ራሱን በክርስቲያን ኃይሎች ከለላ ስር ባደረገ ጊዜ፤ከ1000 የታወቁ ሰዎች የነበራቸውን አቋም መቀየራቸውንና የእርሱን ሃሳብ መቀበላቸውን የሚገልጹ ደብዳቤዎችን አገኘ።

12. ጥሩሩ ምን አይነት ቀለም ነበረው? (ራእይ 9፥17)።

የተለያዩ ቀለሞች ያሏቸውን የብርጭቆ፣የድንጋይና የመሳሰሉ ነገሮች ስብርባሪ አንድ በማድረግ የሚሠሩት ጥንታዊ ስዕል እንደሚያመለክተው ከሆነ እነዚህ ቀለሞች ታዋቂ የኦቶማን ወታደሮች መለያ ነበሩ።

13. ከአፋቸው የወጣው ምንድን ነበር? (ራእይ 9፥17)።

14. በዚህ ሁሉ ጥፋት (መዓት) ሰዎች ንስሃ ገብተው ነበርን? (ራእይ 9፥20-21)

ምእራፍ 11 እስከንደርስ ድረስ ሶስተኛውን ወዮ አናገኝም። ከዛ በፊት በስድስተኛው መለከት ጊዜ የሚከሰቱ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ጉዳዮች በሚቀጥለው እትም እንመለከታለን።

ለተጨማሪ ማብራሪያ ጎድ ኬርስ ከተባለው መጽሐፍ 2ኛው ጥራዝ ገጽ 243-265 ያንብቡ።◆

***በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል***



# የመከራ ዘመን (ክፍል 3)

ታላቁ ተጋድሎ ምዕ.39

ውድ የትንቢት ቃል አንባቢያን፥ ካለፉት እትሞች ጀምሮ «The Great Controversy» ወይም «ታላቁ ተጋድሎ» ከሚለው መጽሐፍ ውስጥ የመጨረሻዎቹን ሰባት ምእራፎች በተከታታይ በማቅረብ ላይ ነን። ይህ መጽሐፍ በ19 መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እና በ20 መቶ ክ.ዘ. መጀመሪያ ላይ በ ኤለን ጂ ኋይት የተጻፈ ሲሆን ወቅታዊ እውነትንና ትንቢትን የያዘ በመሆኑ ለአንባቢያን በረከት ይሆናል ብለን በማሰብ ካለፈው ቀጣዩን መልእክት ይዘን ቀርበናል።

ሰይጣን የእግዚአብሐርን ወገኖች (ልጆች) ስለኃጢያታቸው በሚወነጅልበት ወቅት እነርሱን እስከሚቻለው ድረስ እንዲፈትናቸው ጌታ ራሱ ይፈቅድለታል። በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው ታማኝነት፣እምነትና ጽኑእነት በብርቱ ይፈተናል። ያለፈውን ሕይወታቸውን ሲያስታውሱ ተስፋቸው ይመነምናል፤ምክንያቱም በቀድሞ ሕይወታቸው ብዙ መልካም ነገር እንዳላደረጉ ይመለከታሉና። ደካማነታቸውና ዋቢስነታቸው ሙሉ በሙሉ ይስተዋላቸዋል። ሰይጣን የኃጢያት እድፈታቸው የማይነጻና ተስፋ የሌላቸው መሆናቸውን በመግለጽ ሊያስደነግጣቸው ይጥራል። በዚህ አኳኋን እምነታቸውን አጥፍቶ ለእርሱ ፈተና እንዲሸነፉና በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን ታማኝነት ይተዉ ዘንድ ተስፋ ያደርጋል።

**ኃጢያታቸው ሁሉ እንደተሰረየላቸው ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች ቢሆኑ ኖሮ በደረሰባቸው ስቃይም ሆነ የሞት ፍርድ አይደነገጡም ነበር።**

ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ልጆች ሊያጠፉዋቸው በተዘጋጁ ጠላቶቻቸው ቢከበቡም የሚያሳስባቸውና የሚያስጨንቃቸው ጉዳይ «ያለተናዘዝነው ኃጢያት ይኖር ይሆን? በሕይወታችን ያላስተካከልነው ነገር፤እንደጌታ ቃል ያልሄድንበት ጊዜ ይኖርን? ለዚህ ይሆን እንዴ ጌታ **"የትዕግሥቴን ቃል ስለ ጠበቅህ እኔ ደግሞ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ"** ብሎ የገባልንን ቃል ኪዳን የማይፈጽመው?» የሚለው ሃሳብ እንጂ ስለ እውነት በመቆማቸው ምክንያት ስለደረሰባቸው ስደት አይደለም።

ኃጢያታቸው ሁሉ እንደተሰረየላቸው ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች ቢሆኑ ኖሮ በደረሰባቸው ስቃይም ሆነ የሞት ፍርድ አይደነገጡም ነበር። ነገር ግን በራሳቸው የባህርይ ጉድለት ምክንያት ዋጋቢስ ሆነው ሕይወታቸውን መስዋእት ቢያደርጉ የእግዚአብሔር ቅዱስ ስም ይዘለፋል። እነርሱ በሁሉ ቦታ የአመጻ ሴራ ሲካሄድ ይሰማሉ፣የአመጽ ተግባርም በሁሉ ቦታ ሲካሄድ ያያሉ። ይህ ታላቅ ክህደት በቶሎ እንዲያበቃና የኃጢያተኞችም ክፋት ይፈጸም ዘንድ ነፍሳቸው ትመኛለች። በአንድ በኩል ይህ የአመጽ ሥራ እንዲገታ እግዚአብሔርን ሲማጸኑ በሌላ በኩል ግን ኃያሉን የክፋት ሞገድ በራሳቸው ኃይል ለመቋቋምና ለመመለስ ባለመቻላቸው በራሳቸው ያዝናሉ። «ያለንን ችሎታ በሙሉ ክርስቶስን በማገልገል ሥራ ላይ ብናውለው እና ይበልጥም ከብርታት ወደ ብርታት እየጠነከርን ከሄድን ሰይጣን እኛን ለማሸነፍ ያለው የኃይል ብቃት ያነሰ ይሆናል» የሚል ሃሳብ ይሰማቸዋል።

ቀድሞ ላደረጉት ኃጢያቶቻቸው ንስሃ እንደገቡ በመጠቆምና አዳኛቸውን **«ከእኔ ጋር ሰላም ያድርግ፤ ከእኔ ጋር ሰላም ያድርግ»** በማለት የሰጣቸውን የተስፋ ቃል እንዲፈጽምላቸው በመማጸን ነፍሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት ያስጨንቃሉ። ጸሎታቸው ወዲያውኑ ምላሽ ባለማግኘቱ ምክንያት እምነታቸው አይናወጥም። ምንም እንኳን ከባድ ጭንቀት፣መሸበርና ሃዘን ቢደርስባቸውም፤ልመናቸውን ለእግዚአብሔር ከማቅረብ ወደኋላ አይሉም። ያእቆብ መልአኩን አጥብቆ እንደያዘ እነርሱም የእግዚአብሔርን ብርታት የሙጥኝ ብለው ይይዛሉ። ልሳነ ነፍሳቸውም «ካልባረክከኝ በቀር አልለቅህም» የሚለው ነው።

ያእቆብ ብኩርናውን በማታለል በመውሰድ ያደረገውን ኃጢያት አስቀድሞ ባይናዘዝ ኖሮ እግዚአብሔር ጸሎቱን ባልሰማና ሕይወቱንም በምህረቱ ባላዳነለት ነበር። እንዲሁም የእግዚአብሔር ሕዝብ በፍርሃትና በጭንቀት በሚሰቃዩበት በዚያ የመከራ ጊዜ ትዝ የሚሉዋቸው ከዚህ ቀደም ያልተናዘዟቸው ኃጥያቶች ቢኖሩዋቸው በጠላት ይሸነፉሉ። ተስፋ መቁረጣቸውም እምነታቸውን ያጠፋል፤ ይድኑም ዘንድ እግዚአብሔርን ለመማጸን ልበ ሙሉነት (ሙሉ እምነት) ሊኖራቸው አይችልም። ነገር ግን እነርሱ የዋጋቢስነት ስሜት ከልብ ከተሰማቸው፤የሚገለጹ እና፣ የተደበቁ ስህተቶች (በደል) የላቸውም። ኃጢያቶቻቸው አስቀድሞ ለፍርድ ቀርቦ ተፍቆዋል፤ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ አይታሰቡም።

«በእለት ሕይወታችን የምንሠራቸውን ጥቃቅን ስህተቶች እግዚአብሔር አይቶ እንዳላየ ይሆናል» በማለት ሰይጣን ብዙዎችን ያሳምናል። እግዚአብሔር አምላክ ግን ክፋን ዝም ብሎ እንደማያልፍ በያእቆብ ላይ ባደረገው ድርጊት እንደሆነ ያሳያል። ኃጢያቶችቸውን ቸል ለማለትና ለመሸፈን የሚጥሩ፣ሳይናዘዟቸውና ምህረት ሳያገኙባቸው፣ኃጢያቶቻቸው ከሰማይ መጻሕፍት ሳይሰረዝር ሰፍረው እንዲቆዩ የሚፈቅዱ ሁሉ በሰይጣን ይሸነፋሉ። ዝግጅትን እስከ እግዚአብሔር ቀን ድረስ የሚያዘገይ ማንም ሰው በመከራ ዘመንም ሆነ ከዚያም በኋላ ባለው ጊዜ የመዘጋጀት እድልን አያገኝም። የዚህ አይነት ሰው ሁኔታ ተስፋ ቢስ ነው◆

***ኤለን ጂ. ኋይት***

*(ተከታዩ በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)*

*<u>የሰው ነጻ ምርጫ (ከገጽ 4 የዞረ)</u>*

«ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል። ከዚህ በኋላ ምኞት ጸንሳ ኀጢያትን ትወልዳለች፣ኀጢያትም ካደረገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች» ።

አንድ ክርስትያን ከመልካም ነገር ጋር ጊዜውን ሲያሳልፍ አእምሮው መልካም ምክርን እንዲሰጠው አስተዋጽኦ ያደርጋል «በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፥ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፥ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፥ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን፥ እነዚህን አስቡ» (ፊሊጶስ 4፥8)

ውድ አንባቢ ሆይ፥ አንድ ቀጥተኛ ጥያቄ እንድጠይቅዎ ይፍቀዱልኝ፥ በቀን መጽሐፍ ቅዱስንም ሆነ ሌሎች መንፈሳዊ ጽሑፎችን ለማንበብና ለመጸለይ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳሉ? ይህንን ጥያቄ እራሴን ስጠይቅ ከጌታ የተሰጠኝን የነጻ ምርጫ ስጦታ በመጠቀም በእለት ሕይወቴ ለውጥ እንዲታይ መጣር እንዳለብኝ ይሰማኛል።

እንደ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም ለሚሰጠን አምላክ ክብር ምስጋና ይሁን።◆

## ምስክርነት



# ከወንጌላዊ ባህሩ ወልደ ገብርኤል ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

***ወንድም ባህሩ፥ ለዚህ ቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ስለሆንክ በአንባቢያን ስም አስቀድመን እናመሰግናለን። እሰቲ በመጀመሪያ እራስህን በአጭሩ አስተዋውቀን?***

የተወለድኩትም ያደግኩትም አ/አ ከተማ ተክለሃይማኖት ሰፈር፣በተለምዶ በርበሬ በረንዳ በመባል በሚታወቅ ቦታ ነው። ሶስት እህቶችና ሶስት ወንድሞች አሉኝ። የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ያጠናቀቅሁት በዛው በአካባቢያችን በሚገኝ «አለምማያ» በሚባል ት/ቤት ሲሆን ፣ከዚያም የቀድሞ ስሙ ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ከዚያም እድገት በሥራ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በመባል በሚታወቅ ት/ቤት ነው። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ደግሞ በአዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ነው ያጠናቀቅሁት።

***ሕይወትህን ከጌታ የሱስ ጋር ለመምራት የወሰንከው እንዴት ነበር?***

በልጅነቴ አክስቴ ከሌሎች ወንድምና አህቶቼ ጋር ወደ ቤ/ክ ትወስደኝ ነበር። በተለይ ከአጎቴ ልጆች ጋር አብረን ስለነበር የምንኖረው ወደ ቤ/ክ በሕጻንነቴ እሄድ ነበር። በመሀል ግን ከጓደኞቼ ጋር በነበረኝ ቅርርቦሽ ምክንያት ቀስበቀስ ወደ ቤ/ክ መሄድ በመተው በእነርሱ ተጽእኖ ስር መሆን ጀመርኩኝ። ከዚያም መጥፎ ተግባሮችን፣ፊልም ቤት መግባት፣ጫት መቃም፣መጠጥ መጠጣት የመሳሰሉትን መሳተፍ ቀጠልኩበት። ቢሆንም ለሕይወቴ ትልቅ ለውጥ የሆነኝ በልጅነቴ የተዘራው ቃል ምንግዜም ቢሆን ለመንፈሳዊ ነገሮች ክብደት እንድሰጥ ረድቶኛል። ዘፈን ብወድም መዝሙርንም አላጥላላም ነበር። ቤ/ክ ባልሄድም ወደ ቤ/ክ የሚሄዱትን አከብር ነበር። ስለዚህ አንድ ቀን መጠጥ ጠጥቼ በጣም ሰክሬ ራሴን ስቼ ነበር። የዛን ቀን ምግብ በደንብ አልበላሁም ነበር ፣ጫትም ከጓደኞቼ ጋር ቃምኩኝ። ታዲያ ማታ እቤቴ ስገባ አስመለሰኝ፣ሰውነቴ ደክሞ አል። ቤተሰቦቼ ሲነግሩኝ ግን ደም እንዳስመለሰኝ ነበር የነገሩኝ። እኔም የዛን ቀን የምሞት ነበር የመሰለኝ። ትንሽ ራሴን ሳውቅና መለስ ሲልልኝ ወደ ጌታ እንዲህ ብዬ ጸለይኩኝ፥ «ጌታዬ ሆይ! ዛሬ ብታድነኝ ሙሉ በሙሉ ሕይወቴን ላንተ እሰጣለሁ»።

ከዚያም በመጀመሪያ ለመሄድ ያሰብኩት ወደ ፍልውሃ አድቬንቲስት ቤ/ክ ነው። ምክንያቱም ሁልጊዜ ወደ ስታዲዮም ስሄድ በዚያ ቤ/ክ አጠገብ ነበር የማልፈው። ደግሞም በዛን ጊዜ እኔ በቤ/ክናት መካከል ብዙም ልዩነት ያለ አይመስለኝም ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ አርብ ምሽት ወደ ቤ/ክ ስሄድ የመላላክ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ትምህርት ጨርሰው ላጠናቀቁ የምረቃ ጊዜ ነበር። በዛው እለት ማስታወቂያ ሲናገሩ እኔም ለመውሰድ ወሰንኩኝ። ከዚያ በኋላ ወደ ዓለም አልተመለስኩም። በመጨረሻ ለመጠመቅ ወሰንኩኝ። የሰባተኛ ቀን አክባሪ አድቬንቲስት ቤ/ክ አባል ለመሆን ከረዱኝ እውነቶች አንዱ የሰንበት እውነት ሲሆን የትንቢት መንፈስ መጻሕፍት ደግሞ ብዙ መንፈሳዊ ጥያቄዎቼ መልስ እንዲያገኙ ረድተውኛል።

***በወንጌላዊነት ለረጅም ጊዜ አገልግለሃል፤ስለርሱ ትንሽ ብትለን?***

በመጀመሪያ በፈቃደኛ ወንጌላዊነት በፍልውሃ አደቬንቲስት ቤ/ክ ነው ያገለገልኩት። ከዚያም ከሌሎች ጉደኞቼ ጋር ሆኜ (ዮናታን ተሰማ፣ባህሩ ከበደ፣ አብይ ነጋሽ) በራሳችን ወጪ እስከ ድሬዳዋ ድረስ ሄደን የምናገለግልበት ወቅት ነበር። ከዚያም በኋላ ለሶስት ወር ያህል በሐረር ባለው ቤ/ክ ሲስተር ሸስለማይ ወጪያችንን ችላ። እኔ፣ባህሩ ከበደ እና አብይ ነጋሽ እዚያ ያገልግሎት ጊዜ ነበረን። በዚያ ቦታ ፓ/ር ተመስገን ከነቤተሰቡ የማይረሱኝ ግሩም የሆኑ የጌታ አገልጋዮች ናቸው። በተለይ ሐረር ግሩም ትዝታ ያለኝ አንድ ጊዜ ቤት ለቤት ስንጎበኝ አንድ የደርግ ካድሬ የነበረች ሴት ቤት ከሴትዮዋ እህትና ወንድ ጓደኛዋ ጋር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ጸሎት አድርገናል። ነገር ግን እህቷ ካድሬ መሆንዋን ያወቅነው ከቤት ከወጣን በኋላ ነበር። በእርግጥ አደገኛ ሁኔታ ሊገጥመን ይችል ነበር።



ከሐረር በኋላ ለጥቂት ጊዜ በደብረ ዘይት ከተማ ትንሽ የአገልግሎት ጊዜ ነበረኝ። ከዚያም ረዘም ያለ የአገልግሎት ጊዜዬ የነበረው በመቀሌ ባለው ቤ/ክ ነበር። እዚህ ብዙ የተለየ ልምድ ያገኘሁበት ቦታ ነበር ማለት እችላለሁ። ለምሳሌ፥ በት/ቤት አካባቢ እንደመጽሐፍ ቅዱስ መምህር፣ምክር አገልግሎት ለተማሪዎች፣ ከአስተማሪዎችም ጋር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች ሰጥቻለሁ። በጣም ጥሩ ጊዜ ነበረኝ። በመቀሌ በሚገኘው ወህኒ ቤት በሳምንት አንድ ቀን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ነበረን፤በዚያም ትልቅ የበረከት ጊዜ ነበረኝ። በዛን ጊዜ የተጀመረው የወህኒ ቤት አገልግሎት እስካሁን በመቀጠል ብዙዎች የትንቢት ድምጽን በመከታተል ስለመጽሐፍ ቅዱስ በማወቅና በሕይወታቸው ለውሳኔ የበቁ ጌታን ለመከተል ቁርጥ አላማ ያደረጉ ብዙዎች አሉ። የመቀሌ ቤ/ክ የሴቶች አገልግሎትም በዚህ ታላቅ ተሳትፎ የማልረሳው ትዝታ አለኝ። በየወሩ ሰንበት እለት ምግብ ከየቤታቸው ይዘው በመምጣት እስረኞችን ይጎበኙ ነበር። ይህ ብቻ አይደለም በጉብኝት ጊዜ ከቃሉ በማንበብ የጸሎትም ጊዜ ይወስዱ ነበር። ለዚህ ሥራ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረጉት ምእመናን ነበሩ። ሌላው በወህኒ ቤት አገልግሎት በጣም ከማልረሳው ነገር ቢኖር እዛ ያሉት ወንድሞች ያላቸው የተቀደሰ ሕይወት ነው። ጌታ ለገለጠላቸው ብርሃን ራሳቸውን ከመስጠት አልፈው የበራላቸውን እውነት ለሌሎች ለማካፈል በጣም የተጉ ነበሩ። በቤ/ክ ውስጥ ካለው ግልጋሎት በአካል ተገኝተው መሳተፍ ባይችሉም ነገር ግን እዛው ባሉበት ሆነው ጸሎት በማድረግና ከሚያገኙት ገንዘብ አስራትን በማውጣትና እስከመመስከር ድረስ ነበር ተሳትፎአቸው።

***በአገልግሎት ሕይወትህ በጣም ያስደሰተህ እና በጣም ያሳዘነህ ገጠመኝ ምንድን ነበር?***

አንድ ጊዜ እኔ እና አብሮኝ የሚሠራ ሰለሞን አባይ የሚባል ወንጌላዊ ወደ ማይጨው በመሄድ መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት የሚፈልጉ ሰዎች እንዳሉ አንድ ሰው ነግሮን ከዛ ሰው ጋር ቀጠሮ በማድረግ የምንገናኝበትን ቦታ ወስነን በቀጠሮአችን መሠረት ወደ ማይጨው ሄድን። ከዚያም ያ ሰው ወደነገረን ቦታ ሄደን ሰውዬውን አጣነው፤ብናፈላልግም ማግኘት አልቻልንም። ከዚያም ሰውየውን ለመፈለግ «መሆኒ» ወደሚባል ቦታ በጭነት መኪና ከእቃ ጋር ተሳፍረን ሄድን፤በዚያም ጭራሽ ይህን ሰው ማግኘት አልቻልንም።መኪናው የሚያቦንነው አቧራ ፊታችንን፣ፀጉራችንን ሸፍኖ እኔ ሰለሞንን እያየሁ ስስቅ ሰለሞን ደግሞ እኔን እያየ ይስቃል። በፍለጋ ደክመን የቀጠረንን ሰውየውንም ሳናገኝ ከመሆኒ ወደማይጨው ከተመለስን በኃላ ተስፋ ቆርጠን በመኝታ ክፍላችን ሆነን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ጸሎት እንድናደርግ ወደ ልባችን ሃሳብ አመጣልን። ከዚያም ከመኝታ ክፍላችን በመውጣት በከተማው ስንዘዋወር ከዚህ ቀደም አድቬንቲስት የነበረና በእምነት ትንሽ ደክሞ የነበረ ወንድም አግኝቶን ወደቤቱ ወሰደንና ፀሎት አደረግን። እሱም ከብዙ ሌሎች ሰዎች ጋር አስተዋወቀን። በዚያው ምሽት አልጋ በያዝንበት ሆቴል እራት እየበላን ሳለ አንድ ልጅ ተዋወቅን፤ከዚያም ልጁ ትንቢት ድምጽ የሚባለውን ትምህርት መቀጠል እንደሚፈልግ ፈቃደኝነቱን ገለጸልን። እሱም ከሌላው ጓደኛው ጋር እስተዋወቀን። በዛው አጭር ቆይታችን ብቻ ወደ ስምንት የሚጠጉ ሰዎችን ማግኘት ቻልን። በጣም ትልቅ አስደሳች ጊዜ ነበር። ይህንን ወደ መቀሌ ሄደን ለመመስከር በጣም ጓጓን።

ከአሳዛኝ ገጠመኞች መካከል ደግሞ ልጥቀስ፥ ከሰዎች ጋር ባለኝ ግንኙነቶች ሰዎች ሳያስተውሉኝ ሲቀሩ በጣም አዝናለሁ። አንድ ጊዜ ሶስት በተለያየ ጊዜ የተጻፉ ደብዳቤዎች ደርሰውኝ ነበር። በደብዳቤው ላይ የተጠቀሱት ነገሮች ጭራሽ ጸሐፊው በሃሳቤ የሌለውን ነገር ነበር ጠቅሶ በኃይለኛ ቃል የጻፈልኝ። በተለይ ለአንደኛው ምላሹን ስጽፍለት በጣም ተጠንቅቄ እንዴት እኔን በስህተት እንዳስተዋለኝ አስረድቼ ጻፍኩለት። ከዚያም ያ ሰው በትክክሉ ከተረዳኝ በኋላ ይቅርታ ጠየቀኝ። ሌላው ማንነቱትንና አድራሻውን ያልገለጸ ሰው ነበር። ለርሱ ጸጥ ብሎ ከማለፍ ሌላ መልስ መስጠት አልቻልኩም። ሶስተኛው ግን በወቅቱ ምላሽ መስጠት አስፈላጊ እንዳልሆነ ስላመንኩበት ምላሽ አልሰጠሁም። ምክንያቱም እራሴን አውቅ ስለነበር የምሰጠው መልስ ለውጥ እንደማያመጣ ስላወቅሁኝ ወደ ጌታ ጸሎት ከማቅረብ በስተቀር ሌላ እርምጃ አልወሰድኩም።

***ወንድም ባህሩ አገልግሎትህን አቋርጠህ ትምህርት ጀመርክ፤ይህ እንዴትና የት ነው የሆነው?***

ሙሉ ጊዜዬን ለአገልግሎት ከመስጠት ተቆጠብኩ እንጂ በት/ቤትም ግሩም አገልግሎት ነበረኝ። ከትግራይ ሚሽን ወደ ኩየራ አድቬንተሰት ኮሌጅ ነበር የሄድኩት እዚህ ሁለት ዓመት ሪሊጅን (የሃይማኖት ትምህርት) ከተከታተልኩ በኋላ ለሁለት ዓመት በዚምባብዌ ሱሉሲ ዩኒቨርሲቲ በተጨማሪ የስነመለኮት ትምህርት አጠናሁ።

***ወደ ኖርዌይ አገር እንዴት ልትሄድ ቻልክ?***

ወደ ኖርዌይ የሄድኩት በወንድም ዘውዱ አማካኝነት ሃሳብ ከቀረበልኝ በኋላ ነው። ምናልባት እዚህ ትንሽ ማብራራት የምፈልገው ቢኖር፤ በኖርዌይ የሚገኘው የ «Heart Good Foundation» ከሚመራቸው

*(በገጽ 8 ይቀጥላል)*



# የትንቢት ቃል


Yetnbit Kal
P.O.Box 1749
90006 Nuernberg
Germany

Editors:
Dawit Mehari
Dawit Mengistu

Tel & Fax 0049 - 911- 41 57 89
E-Mail: yetnbitkal@yahoo.com
Web: www.yetnbitkal.org


ይህንን የጽሑፍ አገልግሎት በገንዘብ ለመደገፍ የምታስቡ ሁሉ በዚህ የባንክ ቁጥር መጠቀም ትችላላችሁ።
ለድጋፋችሁ በቅድሚያ ከልብ እናመሰግናለን
እግዚአብሔር ይባርካችሁ!

**IBAN:**
DE32 7605 0101 0002 0599 32
**SWIFT-BIC:**
SSKNDE77

ይህች «የትንቢት ቃል» የምትለው የአድቬንቲስት መጽሔት በጀርመን አገር ተዘጋጅታ ትወጣለች። አላማዋም በአገራችንና በተለያዩ አህጉራት የሚገኙትን ወገኖቻችንን ለየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ለማዘጋጀት ነው። ምንም ዋጋ የማይከፈልባት በነጻ የምትላክ እንደሆነች ልንገልጽልዎ እንወዳለን። ስለዚህ ለእርስዎም ሆነ ለሌሎች ጽሑፉ እንዲደርሳቸው ለሚፈልጉት ሰዎች አድራሻዎችን ቢያሳውቁን መጽሔቱን እንልካለን።

በዚህች መጽሔት መልእክት ተባርከው እንደሆነና አስተያየትም ሆነ ጥያቄ ካለዎ ሃሳብዎን ቢገልጹልን በጣም ደስ ይለናል።

***ወንጌላዊ ባህሩ ....(ከገጽ 7 የዞረ)***

አንዱ የ «Europian Bible School» (የአውሮፓ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤ) ነው። በዚህ ት/ቤ ይማር የነበረው ዘውዱ ስለአላማው ሲገልጽልኝ እኔም መማር የምፈልግ እንደሆንኩኝ ፈቃደኝነቴን ገለጽኩለት። በመሠረቱ የዚህ ት/ቤ መስራች ዶ/ር አርቪድ ሆጋንቢክ በኢትዮጵያ ውስጥ በደብረታቦር ከተማ ተመሳሳይ የሆነ ት/ቤት ለመክፈት አላማ ስለነበራቸው ለዛም አላማ ነበር እኔም ሌሎችም ኢትዮጵያውያን እዛ ሄደን ለመማር የተጋበዝነው።

***ለሚቀጥሉት ዓመታት ያለህ የሕይወት አላማ ምን ይመስላል።***

ትዳር መመስረትና ጌታ ባዘጋጀልኝ ቦታ እና ጊዜ ሁሉ እሱን ለማገልገል ነው።

***እስካሁን ካሳለፍከው የሕይወት ልምድ አንጻር ለአንባቢዎች የምታስተላልፈው ካለህ?***

ኢሳያስ 42፥16 ን መሠረት በማድረግ ጌታን ለማገልገል ስንቆም ሰዎች ሊከዷችሁ ወይም በስህተት ሊያስተውሏችሁ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ ለጌታ በምትወስኑት ውሳኔ ነገሮች ጭለማ ሊሆንባችሁ ይችል ይሆናል። ግን የጌታ ተስፋ ዘወትር አይጨልምም። ቢገባችሁም ባይገባችሁም፣ ብታስተውሉትም ባታስተውሉትም በጌታ ተስፋ ጽኑ! በእርሱ ዘንድ ቆዩ!። ጨለማውን ወደ ብርሃን፣ ጠማማውን በማቅናት የሚያስደንቅ ተአምር የሚሠራ ጌታ ነው። ተስፋ አትቁረጡ! በመጨረሻም ሶስት ነገሮችን እንድመክራችሁ ፍቀዱልኝ፥ 1ኛ) ጸልዩ! 2ኛ) ጸልዩ! 3ኛ) ጸልዩ!። ጌታ ይባርካችሁ!

***ውድ ባህሩ፥ እናመሰግናለን። አንተንም ጌታ ይባርከህ!*** ◆

## ደብዳቤዎች

በእግዚአብሔር የተወደዳችሁ የትንቢት ቃል መጽሔት አዘጋጆች!
እግዚአብሔር በእናንተ በኩል እየሠራ ስላለው መልካም ሥራ አምላኬን አመሰግናለሁ። ከዚህ በፊት ባላውቃችሁም በጓደኛዬ በኩል ከእናንተ ጋር ለመተዋወቅ በመብቃቴ በጣም ደስ ብሎኛል። ሌላው በጣም ደስ ያለኝ ነገር ቢኖር እኔ ወደ 7ኛ ቀን አክባሪ አድቬ ቤ/ክ የመጣሁት በቅርቡ ነው። ያገኘሁት በረከት ግን ከ እስከ የሚባል አይደለም። ይህንን በረከት ሌሎችም እንዲያገኙት የበኩሌን እያደረግሁ ነው። እግዚአብሔር እንዲረዳኝ በጣም አድርጋችሁ ጸልዩልኝ። አጋዥ ጽሑፎችንም ላኩልኝ። በኢሜይል የምታሰራጩትንም ወቅታዊ እውነቶች አጋሩኝ። ለወደፊት ብዙ ነገር እጽፍላችኋለሁ። ብዙዎችን አስከትላችሁ በእግዚአብሔር መንግሥት የምትሆኑበትን የተትረፈረፈ የእግዚአብሔር ሃይል ዘወትር ከእናንተ ጋር ይሁን። የጌታ ጸጋ ይብዛላችሁ።

***ባቢሶ ባንጫ ከወላይታ ሶዶ***

በየሱስ ክርስቶስ ሰላም ለእናንተ ይሁን በማለት ሰላምታዬን በማስከተል ላመሰግናችሁ የምፈልገው ነገር አንደኛ፥ በእውነቱ እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር እንዳለው ሁሉ እናንተም በመንፈስ እንዳላችሁ እና እኛን ስለማትረሱን በጣም አደንቃችኋለሁ። በየጊዜው በምታወጙት መጽሔት በማጽናናታችሁ ጌታ ኃይሉንና ብርታቱን ይስጣችሁ። እዚህ እኔ ጋር ላሉት ወንድሞችና እህቶች አድራሻችሁን ሰጥቼአቸው እነርሱም ለማግኘት ችለዋል። ባለንበት አካባቢ ለጊዜው ቤ/ክ ባይኖረንም የላካችሁልንን መጽሔት በማንበብ እየተጽናናን እንገኛለን። በእርግጥ እናንተ ለእኛ የምትልኩት መጽሔቶች ዋጋ ያላቸውና ከፍተኛ ወጪ እያደረጋችሁ እንደምታሳትሙ ይገባናል፤ያቅም ማነስ ጉዳይ ስለሆነብን ነው እንጂ ብንተባበራችሁ ደስ ይለን ነበር። ሌላ የምንለው ስለሌለ ጌታ በረከቱን እንዲሰጣችሁ እንጸልያለን። ወገኖቼ በርቱ! በርቱ! ለምጽአቱ በቅተን ለመገናኘት ብሎም በአዲሲቱ የሩሳሌም ተገናኝተን ለመኖር ያብቃን። ጌታ ይባርካችሁ!

***ወንድማችሁ ታዬ አበራ ለማ***
***ከጋሞ ጎፋ ሳውላ***

**ወቅታዊ ዜናዎችን ይዞ በኢሜይል የሚሰራጨው የትንቢት ቃል ኒውስሌተር በየሁለት ወሩ እንዲደርስዎ ከፈለጉ በሚከተለው አድራሻችን ይጻፉልን፣እንልክልዎታለን፥**

**newsletter@yetnbitkal.de**
**yetnbitkal@yahoo.com**

**ውድ አንባቢያን!**

የምስክርነት አምዳችን እግዚአብሔር ሰዎችን እንዴት አድርጎ ከድቅድቅ የኃጢያት ጨለማ አውጥቶ ወደሚደነቅ ብርሃን እንዳመጣቸውና ትእዛዙን ከሚጠብቁት እንዲሁም የሱስን በማመን ከሚጸኑት ሕዝቡ ጋር እንደቀላቀላቸው የምናሳይበት አምድ ነው። የእርስዎንም ታሪክ ጌታ የሱስ እንዴት እንደቀየረውና የሰማይ ቤት ወራሽ እንዲሆኑ እንዳደረገዎ ለአንባቢያን ለማሳወቅ ፈቃድዎ ከሆነ ምስክርነትዎን በጽሑፍ ቢልኩልን በዚህች መጽሔት አማካኝነት ለብዙዎች በረከት ልናውለው እንችላለን።

አዘጋጆች